DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

## SY25-26 እና SY26-27 Bard High School Early College DC፥ የቅበላ ሂደት መመርያዎች

ለክፍል፡ 9-11

**ማስታወሻ፥** ይህ መመርያ ለSY25-26 እና SY26-27 የተማሪ ቅበላ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**ስለ Bard High School Early College DC የቅበላ መስፈርት**: በ Bard High School Early College DC (Bard DC) ውስጥ ተነሳሽነት፣ ምሁራዊ የማወቅ ፍላጎት እና ትምህርታዊ ተግዳሮት ላይ መደነቅን የሚያሳዩ እና ቀደም ባለ እድሜያቸው ወደኮሌጅ ትምህርት የመግባባት ጉጉት ያላቸውንምሁራን ማግኘት እንፈልጋለን።

**ስለ Bard High School Early College DC የቅበላ ሂደት**: Bard DC ውስጥ ያለን የቅበላ ሂደት ለ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የጽሁፍ ግምገማን፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሁለት የድጋፍ ደብዳቤዎችን እና የውጤት መግለጫ ካርድ ግምገማን ያካትታል። 11ኛ ክፍል፣ የውጤት መግለጫ ካርድ እና የትራንስክሪፕት ግመገማ አለ። ለማንኛውም አመልካች እያንዳንዱን የቅበላ ክፍል ታሳቢ የምናደርግ ሲሆን፣ ሁሉም አመልካቾች በተቀመጠ መስፈርት መሰረት ውጤት ተሰጥቷቸዋል። የትኛውም አንድ የቅበላ መስፈርት ወይም ክፍል ብቃትን ለመወሰን ብቸኛ መለኪያ አይሆንም። ለቅበላ ከግምት ውስጥ ለመግባት ሁሉም አመልካቾች ቃለ መጠይቅ ማድረግ እና ጽሁፍ መጻፍ አለባቸው።

እያንዳንዱ ክፍል ከታች ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ውጤት ተሰጠቶት ይመዘናል። ለቅበላ ከግምት ውስጥ ለመግባት አመልካቾች በድምሩ ከአጠቃላይ 17 ነጥብ ቢያንስ 12 ነጥብ ማግኘት አለባቸው። ከ12 በታች ነጥብ ያመጡ አመልካቾችም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ ባገኙት ጠቅላላ ነጥብ መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።

| የቅበላ ክፍል | ክብደት | ማሳሰቢያዎች |
|---|---|---|
| የሪፖርት ካርድ ግምገማ (GPA ይጨምራል) | (3/17 ነጥብ) | Bard DC እንደ የሪፖርት ካርድ ግምገማ አንድ አካል ሆኖ የትምህርት ውጤቶችን (GPA) ይገመግማል። አመልካቾች የSY23-24 የመጨረሻ እና የSY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት ካርዳቸውን ማቅረብ አለባቸው። የሚፈለግ ዝቅተኛ GPA የለም፣ ነገር ግን ማመልከቻው ለቅበላ ከግምት ውስጥ እንዲገባ ሁለቱም የሪፖርት ካርዶች መቅረብ አለባቸው።<br><br>አብዛኛውን ጊዜ በኛ ፕሮግራም ውስጥ በጣም ስኬታማ የሆኑት አመልካቾች በ2.0 ወይም ከዚያ በበለጠ GPA የሚገቡት ሆነው አግኝተናቸዋል። ሆኖም ግን፣ ዝቅተኛ GPA ያላቸው አመልካቾችም ትክክለኛው ድጋፍ እና ስልቶች ተደርጎላቸው ስኬታማ መሆን እንደሚችሉ ማወቅ ችለናል። |
| ቃለ መጠይቅ | (5/17 ነጥብ) | Bard DC ለኛ ፕሮግራም ጥልቅ ፍላጎት፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ የለውጥ ወኪል የመሆን ፍላጎት ያላቸው እና የመማር ፍቅር ያላቸውን አመልካቾችን ለይቶ በማወቅ በጥብቅ ያምናል። ገላጭ የሆነ እና አዳዲስ ነገሮችን ለመማር ደስተኛ የሆነ ተማሪ እንፈልጋለን።<br><br>በቃለ መጠይቁ ወቅት፣ የBard ቡድን ከፍተኛ የሆነ የማወቅ ፍላጎት እና የመማር ጉጉት ያላቸውን ተማሪዎች ማግኘት ይፈልጋል። ከፕሮግራማችን ያስደሰታቸው ምን እንደደሆነ እና ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገጥማቸውን ተግዳሮት እንዴት መወጣት እንደሚችሉ ማወቅ እንፈልጋለን። በተጨማሪም ራሳቸውን እንዴት እንደሚያዩ እና ግጭቶችን ወይም ከባድ ሁኔታዎችን እንደሚፈቱ ማወቅ እንፈልጋለን። በመጨረሻም ስላላቸው ጥልቅ ፍላጎትና ምኞት፣ ግብ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ምን ማሳካት እንደሚፈልጉ መስማት እንፈልጋለን።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ምክንያቶች፣ ለ SY25-26 ቃለመጠይቆች በኦንላይን ሊደረጉ ይችላሉ። |

| | | |
|---|---|---|
| በቦታው በመገኘት የሚቀርብ የጽሁፍ ድጋፍ (በቃለ መጠይቁ ወቀት የሚሞላ) | (5/17 ነጥብ) | ልክ እንደ ቃለ መጠይቁ፣ የሚቀርበው ጽሁፍ ተማሪው በፕሮግራማችን ላይ ያለውን ፍላጎት፣ ለማህበረሰብ ያለውን ቁርጠኝነት እና የወሳኝ አስተሳሰብ ችሎታዎችን ለመመዘን ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ድጋፍ በቃለ መጠይቁ ወቅት በቦታው ይሞላል።<br><br>ምንም እንኳን አመልካቾች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቆይታቸው ሁሉ ውስጥ በመደበኝነት እንደሚጽፉ የሚጠበቅ ቢሆንም፣ የዚህ የጽሁፍ ድጋፍ መስፈርት እንደ ሰዋወሰው እና ቃላት ባሉት ቴክኒካዊ የጽሁፍ ክህሎቶች ላይ አያተኩርም። መመርያው የሚያተኩረው ተማሪዎች ለድጋፉ በሚሰጡበት ሁኔታ ላይ ነው። የጽሁፉን ግልጽነት፣ ጥልቀት እና አይነተኝነት ይገመግማል። ከፍተኛ ውጤቶች የተሰጡት ጠንካራ ተሳትፎን፣ ግልጽ አተያዮችን እና ፈጠራን ለሚያሳዩ በአግባቡ ለተዘጋጁ ምላሾች ነው።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ምክንያቶች፣ ቃለመጠይቆች (በምዘና ቦታው ላይ የጽሑፍ ናሙና ማጠናቀቅን ይጨምራል) ለ SY25-26 በኦንላይን ሊደረጉ ይችላሉ። |
| የድጋፍ ደብዳቤዎች | (4/17 ነጥብ) | Bard DC ተማሪው በትምህርት ቤት ስላለው ልምድ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት እና ለውጤት መግለጫ ካርዳቸው አውድ ለመስጠት የድጋፍ ደብዳቤዎችን ይጠቀማል።<br><br>Bard DC ሁለት (2) የድጋፍ ደብዳቤ ይጠይቃል። በተጠየቀው መምህር የተሞላው አንድ ብቻ ከሆነ፣ ተማሪውን በቀረበው አንድ የድጋፍ ደብዳቤ ብቻ እንመዝነዋለን። የቀረበ የድጋፍ ደብዳቤ ከሌለ፣ ትምህርት ቤቱ ነጥቦቹን ለቃለ መጠይቅ እና ለጽሁፍ ብቻ ይበትናቸዋል። የተጣመረው ውጤት በሂደቱ ውስጥ ወዳሉት ቀጣይ ደረጃዎች የማለፍ ብቁነትን ይወስናል።<br><br>አመልካቾች እና ቤተሰቦቻቸው በነሱ ስም የድጋፍ ደብዳቤ ከሚሰጡ ግለሰቦች ጋር እንዲከታተሉ እና በተቻለ መጠን ስለተማሪው የተሟላ ምስል ማግኘታችንን እንዲያረጋግጡ በጥብቅ እናበረታታለን። |
| **12 ነጥብ ወይም ከዚያ በላይ ያገኙ አመልካቾች በሙሉ ለቅበላ ብቁ ይሆናሉ።<br>ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ ባገኙት ጠቅላላ ነጥብ መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።** | | |